# የጎንደር ሕብረት

[gonderhibrert72@gmail.com](mailto:gonderhibrert72@gmail.com) /website: www.gonderhibret.org


ይድረስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

ጎሕ ቁጥር #9

## የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር በጎንደር የከፈተዉ የዕብሪት ጦርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ በባርነት ለመግዛት ያለመዉ ቅዠት ነዉ

በቅድሚያ፤ የፍርሃት ጨለማን ደፍረዉ የባንዳ ኢጋዚ አፋኞችን ዘርረዉ መስዋዕትነት ከፍለዉ ክብር ላላበሱን የጎንደር ኢትዮጵያዊ ሰማዕታት ጀግኖችን ስም እንዘክራለን፦

ጀግና አቶ ሲሳይ ታከለ

ጀግና አቶ ሰጠኝ ባብል ከበደ

ጀግና አቶ ደሳለኝ

ጀግና አቶ ጌታዉ ጎዳናዉ አምዴ

ሌሎችም ስማቸዉን ያላገኘናቸው ጀግኖች ሁሉ ስማቸዉ በጎንደር/በኢትዮጵያ የታሪክ የወርቅ መዝገብ እንደሚሰፍር ስንገልጽ ከፍ ባለ ኩራት ነዉ።
የዛሬዉ መግለጫችን የሚያተኩረዉ የትግራይ ነጻ አዉጭ ዘረኛ ቡድን የሚያካሂደዉን በጎንደር ክፍለሃገር የተፈጸመዉን አፈና ለመቋቋም የህብረት ተሳትፎ ጥሪያችን ለማስተላለፍ የታሰበ ነዉ። መላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚያዉቀዉ፤ የወልቃይት ጠገዴን/ጠለምት ህዝብ የ30 ዓመታት የዘር ማጥፋትና ማጽዳት ግፍ ተፈጽሞበታል። በተመሳሳይ መልኩ በሌሎችም የኢትዮጵያ ምድር ያሉ ዜጎች ሁሉ የወያኔ እስረኛ ከሆኑ 25 ዓመታት ተቆጥሯል።
በወለጋ፤ በጋምቤላ፤ በአፋር የመሬት ቅርምት ሰለባ የሆኑ ወገኖቻችን፤ በአዲስ አበበባና አካባቢዊ ቤታቸዉ ፈርሶ ሜዳ ላይ ዝናብ እየወረደባቸው የተበተኑና ስደተኛ የሆኑት፤በሃረር ፤በጎንጎፋ፣ በኤሊባቡር በአሪሲ፤ በባሌ፤ በሃረር ፤ በኡጋዴን፤ በትግራይ፤ በጎጃም መተከል በወያኔ ኢጋዚ የሚገደለዉ፤ የሚታሰረዉ ፤የሚሰደደዉ በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊያን የተዋረዱበት ዘመን ቢኖር በወያኔ ዝመን ነው።
ይህ ሊሆን የቻለዉ አዉቀንም ሆነ ሳናዉቅ ለክፍፍል የዳረገንን የዘር ፖለቲካ አስተናጋጅ በመሆናችን ብቻ ነዉ። ወያኔ ያመጣዉ የብሄር ብሔረሰቦችን መብት በማስከበር ስም ህዝቦቿንና አገሪቱን ለማጥፋት የተጠቀመበት ስልት እንደሆነ ገሃድ እየሆነ መቷል። በአፍራሽ ጽንሰሃሳብ እያወናበዱ አገር በቀል ቅኝ ገዥነትን ካነገሱ 25 ዓመት አስቆጥረዋል። በተቀደሰችና በዓለም ዝናን ባተረፈች አገራቸዉ ኢትዮጵያዉያን ተዋርደዉ እየኖሩ ነዉ። ጸረ ኢትዮጵያ የሆነው ቡድን የዉጭ ዜጎችን ተከብረዉ እንዲኖሩ የፍቃድ ወረቀት በመስጠት ላይ ይገኛል። የአገራችን መሬት ቆርሶ ሰቶ የበአድ ወታደር በማስፈር ላይ

ተሰማርቷል። የአገሩን ሰላምና ዴሞክራሲ ሳያስከብረ በርዳታ ሰጭ ድርጅቶች አይን ስላማዊ ለመምሰልና የውጭ ምንዛሬ ለማገኘት ሲል የአገሪቱን ወጣት ዜጎች ወደ ሌላ አገር እየላከ ደማቸውን በከንቱ ያፈሳል። በሌላ በኩል የተፈናቀለዉ ወገናችን ለስደት ተዳርጎ በተለይም ለአገራችን አምራች ሊሆን የሚችለውን ወጣቱን የሰዉ ሃይል በማሠደድ በባዕዳ አገር በየ እስር ቤቱ የሚማቅቀውና በየቀኑ እራሱን የሚያጠፋዉ ቁጥርም መጠን እየጨመረ ነዉ።

ዉድ ኢትዮጵያዊያን!

በታሪክ አጋጣሚ አገር በቀል ወራሪ ቡድን በኢትዮጵያ አገራችን ተፈጥሯል። የኢትዮጵያን ሕዝብ በመጉዳት የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር ለአለፉት 25 ዓመታት ተከታታይ ሃገራዊ ዉርደትና ዉድመት ፈጽሟል። ይህ ከዉጭ ወራሪወች በባሰ መልኩ በአገሪቱ አራት ማዕዘን በነገድ ለማፋጀት የአንድ ዘር ድርጅት 82 ነገዶች የሚኖርባት በቋንቋና በባህል ትስስር የተዋበች ኢትዮጵያን ገጽታ አጥቁሮ፤ ህዝቡ በፍቅር የኖረበትን ሃረግ ለመበጣጠስ እና በመሳሪያ አፈሙዝ ለመግዛት ቆርጠዉ በጭፍን በመቀጠላቸዉ ወደዘር ግጭት ለመዘፈቅ ከምንጊዜዉም በበለጠ አፋኙ የትግራይን ልዩ ሃይል አሰማርተዋል።

ሰሞኑን በታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ የወልቃይት ጠገዴ/ጠለምት የማንነት ጥያቄ የሚያራምዱ ታጋዮችን አንደበት ለማፈን ከክልሉና ከጎንደር ዞን እዉቅና ዉጭ በወያኔ የፌደራል የማጭበርበሪያ ወረቀት ህገወጥ አፈና ሲሞክሩ አጋዚወች ለዉርደት ተዳርገዋል። የጎንደር ህዝብ፤ የወልቃይት/ጠገዴ፤ጠለምትና የአርማጭሆ ጀግና የወልቃይት የማንነት ጥያቄ አቅራቢ የኮሚቴ አባላት የህዝብ ተወካይ መሆናቸዉን በጀግንነት ከጎናቸዉ ቆሞ አረጋግጣል።

ከአሁን በኃላ የትግራይ አፋኝ ቡድን ጎንደርን ለማጥፋት እንጅ ለማስተዳደር እንደማይሻ እርግጠኛ በመሆን አፋኙን ቡድን ለመጋፈጥ ቆርጦ ተነስቷል። መላዉ የአማራ ህዝብም ከእንግዲህ አፈናን፤ ዉርደትን ላለመቀበልና ለሙብቱ ለመታገል ዝግጁ ሁኗል። በጎንደር ህዝብ እምነት ከወያኔ ከዉሸትና አፈና ሌላ የሚጠብቀዉ የለም። የእርቅና ሰላም ጨዋታ ለወያኔ የመፍትሄ ሳይሆን ሲዳከም ጊዜ ገዝቶ የሚያጠቃበት ስልት ብቻ ነዉ። ለሆዳቸዉ ባደሩ ካህናት ታቦት አሸክሞ በርቅ ስም ተዘጋጅቶ ለማጥቃት በጓሮ የሚያካህደዉ የሰላም ይዉረድ ሴራ ጊዜ ያለፈበት ጨዋታ ነዉ። የቤተ ክህነት አባቶች እርፈዉ እንዲቀመጡ በሕዝብ ሊነገራቸው ይገባል። ወያኔዎች ሲሚዳከሙ ጊዜ ለመግዛት ሽማግሌ ጎተታ ልማዳቸዉ ነዉና የአልገዛም ባይነት ህዝባዊ አመጽ ያለማቋጥ መቀጠል አለበት። በዳንሻና በሰሮቃ በሽምግልና ስም ሕዝቡን በማዘናጋት ወያኔ ብዙ ጉዳት እንዲያደርስ አድርገዋልና የአገሬ ጀግና ከአሁን በኋላ እንዳትዘናጋ።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!**

ወያኔ በተፈጥሮዉ ህዝብን ለማዳመጥ ህሊና ያልፈጠረለት፤ እርቅ ሲሉት በፍርሃት የሚተረጉም ይልቁን ለማጥቃት የሚዘጋጅ፤ ህዝብና መንግስት፤ ህግና ፍትህ ለሚባል ነገር ለትርጉሙም ሆነ ለተግባራዊነቱ እጅግ ጸረ ፍትህ አዉሬ ቡድን ነው። በመሳሪያ ብቻ ጦርነት ፈጣሪ ነኝ ብሎ በትቢት የተወጠረ በአጋዚ ጦር ብቻ የተማመነ ከህዝብ የሸሸ ድርጅት ነዉ። ይህን ባህሬውን ደግሞ የሚያስተነፍስ የህዝባዊ አመጽ እዬመጣበት መሆንን በማወቁ ጎንደርን ወደዘር ግጭት ለማስገባት የሚያካሂደዉን ፕሮፖጋንዳ የመላዉ ኢትዮጵያ ህዝብ ተገንዞብና አውቆ በአንድነት ቆሞ ይህን ጨካኝ መንግስት እንዲያሰናብተዉ በጥብቅ እናሳስባለን።

ባለፉት መግለጫወቻችን እንዳስገነዘብነዉ የወልቃይት ጠገዴ/ጠለምት የጎንድር/የአማራ የማንነት ጥያቄ በማስፈራራትም ሆነ በሽንገላ በትግራይ አስተዳደር ዉስጥ በሃይል ታፍኖ መኖር እንደማይችል ጀግናዉ የጎንደር ሕዝብ ድምጹን አሰምቷል። ተግባራዊ ሥራም በስፋትና በቆራጥነት ጀምሯል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአስቸኳ ከጎኑ ሊቆም ይገባል። ይህ ዘረኛ መንግስት ከስልጣን መዉረድ አለበት ። ካለፈዉ ስተቱ ጭራሽ የማይማረዉ በሙስና የተዘፈቀ ድርጅት ከእንግዲህ የአማራን ህዝ በሃይል እገዛለሁ ማለት ቅጀትና ከንቱ ነዉ።

የወልቃይት/ጠገዴና የጠለምት የማንነት ተሚጋቾች ብዕር አንስተዉ አለ በተባለዉ ህገመንግስት ተማምነዉ አሥራ አንድ ጊዜ አዲስ አበባ ተመላልሰዉ አንድም ምላሽ ሳያገኙ ፍትህ የተነፈጋቸዉ ንጹህ ዜጋዎችን አሸባሪ ናቸዉ ብሎ አኬል ዳማ መስራት ከበደል ላይ በደል ነዉ። የወያኔ ገዥዎች እራሳቸዉ ብጥብት ፈጥረዉ ለጠፋው ህይወትና ንብረት ዋና ተጠያቂዎች ናቸው። አሁንም ተበዳዩ የጎንደር ሕዝብ/የአማራ ክልል ይክፈል ከማለት አልተቆጠቡም። እኛ የምናስተላልፈዉ መልክት እንደ ከዚህ ቀደሙ ማንም ኢትዮጵያዊ  የትም ሂዶ ሰርቶ የመብላት መብቱ የተከበረ ነው። ስለዚህ ንጹህ ትግርኛ ተናጋሪዎችም ጎንደር ሰርቶ የመኖር መብት አላቸው ። ሕዝባችን ማተኮር ያለበት በወያኔዎችና በግብረ አበሮቻቸው ላይ ብቻ ይሆን።

ወያኔወች በኤርትራ ህዝብ ላይ የሰራችሁትን የዘር ማጽዳት ድርጊት ማስታወስ ግድ ይላል። በኢትዮጵያዊነት ያመኑ ኤርትራዊያንን የሻቢያን ካርድ እንዲይዙ እና በኤርትራ መገንጠል እንዲሳተፉ አስገድዳችሁ አዲስ አበባ ኗሪ ወገኖቻችን መገንጠልን ምረጡ በሚል ግዳጅ አስፈርማችሁ  የኤርትራን መንግስት ስትከዱ 75,000 የኤርትራ ደም አላቸዉ የተባሉ አማራወች ጭምር ሃብታቸዉን ዘርፋችሁ በርሃ እንደጣላችሁ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነዉ።

አሁን እንደገና ለሙብት ታጋይ ጎንደሬዎችን በጀምላ ለመወንጀል  በኤርትራ የሚደገፉ አሸባሪወች የሚለዉ ዉሸት አይናችሁን ጨፍኑ ላሞኛችሁ የአኬል ዳማ መዝሙር ከእንግዲህ የተሰለቸ ዉድቅ ፖለቲካ ነዉ። ለወያኔ የተሻለዉ አማራጭ ህዝብ አሸናፊ መሆኑን አምኖ  ስልጣንን ለህዝብ ማስረከብ ብቻ ነዉ፤ ከዚህ ያለፈ የአፈና እርምጃ አደጋዉና መዘዙ ብዙ ነዉ። የጎንደር ሕዝብ እግዚአብሔርን እንጂ ወያኔን አይፈራም። ወልቃይት ተገዴም/ጠለምት የጎንደር/የአማራ መሬት ነዉ። በጉልበት ለመዉሰድ የሚሞከር ሁሉ በቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች ይመለሳል

**ለመለዮ ለባሹ ሰራዊት**

ባለፉት መንግስታት የአገር ዳር ድንበር ለማስከበር  እና ለህዝባችሁ ሰላምና ክብርን ለማጎናጸፍ በዉትድርና ሙያ ገብታችሁ ብዙ መስዋትነት መክፈላችሁን የኢትዮጵያ ህዝብ አይረሳዉም፤ ነገር ግን የመሪነት ብቃት የሌላቸዉ የትናንት መሪወች እንደዛሪወቹ የህዝብን ብሶት ባለመስማታቸዉ ዘመናዊ ወታደራዊ ሙያ ክህሎት ያላቸዉ በምድር ጦር በአየር ሃይል፤ በባህር ሃይል፤ የፖሊስ ሰራዊት አሁን በማገልገል ላይ ያለዉ ሰራዊት ጭምር ለዉርደት ተዳርጓል። ለዚህም ምሳሌ በአሁኑ ሰዓት መሪ ያጣዉ ሰራዊት የጋምቤላ ወገኖቻችን በሱዳን ወታደር 200 ተገለዉ 150 ታፍነዉ የተወሰዱት እና  2000 የጋማ እና

የቀንድ ከብቶች መዘረፍ በወያኔ ሴራ እንደሆን ሁሉ አዉቆታል። በጎጃም/ቢሻንጉል በመተከል፤ በጎንደር በሽንፋ፤ በመተማ፤ በስናር የተገደሉት እና ታስረዉ የተወሰደቱን ወገኖቻችን ስናስብ አሁን ያለዉ ሰራዊት ያፈረበት ታሪክ ነዉ።

መለዮ ለባሹ ሰራዊት! በያለህበት ሁሉ የህዝብ አመጹን ተቃላቅለህ ያገራዊ ክብር መለዮህን ዛሬ ልበሰዉ። ያካበትከዉን ወታደራዊ ሙያ እድሜ ሳይገድበዉ ተሳተፍ። ከመካከልህ ጀግና የትግል መሪወችን መርጠህ አምነህ ተከተላቸዉ። የአካል እና የመንፈስ ጥንካሬ፤ የአገራዊ ፍቅር ያለዉ ሁሉ እድሜ፤ ዘርና ጾታ ሳይለዉ በትግሉ ሜዳ እንዲሰማራ ጥሪያችን እናቀርባለን።

**በአገርቤት ለሚንቀሳቀሱ የወያኔ ተቃዋሚ ድርጅቶች፤**

ህግን የማያከብር መንግስት ህጋዊ ፍቃድ ሊሰጥ አይችልምና በህዝባዊ አመጽ ድምጽ የፍህራት ሸማን ቀዳችሁ ትግሉን በብቃት እንድትመሩ ታሪካዊ ሃላፊነት አለባችሁ። ቆራጥ የትግል ጓዶቻችሁ በስር ቤት እየማቀቁ፤ በጋለ ብረት እየተጠበሱ፤ ሰልፍ ለመዉጣት ፍቃድ ተከልክለናል የሚለዉ ምላሽ ህዝባዊነት የለዉም። በተለይ በአሁኑ ሰዓት ተቀባይነት የለዉ። ከትግል ሞት አምልጦ ህዝብን ነጻ ማዉጣት ስለማይቻል ምሩት ወይም ትግሉን ለሰፊዉ ህዝ እራሱ መርጦ እንዲመራ ተዉለት፤ በሃሳብ የሚከፋፍል መግለጫ እንዳትሰጡ አደራ እንላለን። ቢያንስ በዘረ መስመር እንዲራመድ ህዝቡን ቀፍድዳችሁ አትያዙት። ወያኔ የፈጠረዉ ሃገራዊ ዉርደት በቆራጥ ህዝባዊ ትግል መለወጥ አለበት።

በዉጭ ለሚታገሉ የተቃዋሚ ድርጅቶችና አገር አፍቃሪ ኢትዮጵያዉያን

በስደት አለም ሁናችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ከአምባ ገነኖች የጭቆና ቀምበር እንዲላቀቅ ጸሃይና ብርድ ሳይገድባችሁ በአደባባይ ድምጻችሁን በማሰማት፤ በዲፕሎማሲ ዘረኛዉን ስርዓት በማጋለጥ፤ በስደት የተጎዱ ኢትዮጵያዊያን ወንድም እህቶቻችን በመርዳት በተለያየ መልኩ አገር ቤት ያለዉን ትግል በገንዘብ፤ በቁሳቁስና በሞራ ድጋፊፍ በመስጠት የተደረገዉ የብዙ ዓመታት አስተዋጽኦ በኢትዮጵያ ህዝብ ልብ የተጻፈ ነዉ። በታሪክም ማህደርም ተዘግቧል። በስደት ያሉ የሃይማኖት አባቶ በአደረጉት ትግልም ለህዝባችን ነጻነት ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል። የጎንደር ህብረትም የዚህ እረዥም ትግል ዉጤት ያፈራዉ የትግል አካል ነዉ ብለን እናምናለን። ወያኔ ያጨቀየዉን የዘር ፖለቲካ ለማጽዳት ትኩረታችን ሁሉ ለድርጅት ሳይሁን ለኢትዮጵ ሕዝብ ፍትህ የሚያጎናጽፍ ተግባራዊ እርምጃ የምንወስድበት ምዕራፍ ላይ ደርሰናል። ስለሆነም፤ ያሉንን ጥቃቅን ልዩነቶች ወደጎን በማድረግ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስንል በአንድነት ተባብረን ወያኔን ከስልጣን ለማስወገድ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአሁን ሰዓት በአንድ ድምጽ እያካሄደ ያለዉን የነጻነት ትግል ያለማቋረጥ እንድንደግፍ የጎንደር ህብረት ጥሪዉን ያቀርባል።

**<u>አስቸኳይ ጠቃሚ የሕዝባዊ ትግል መልከቶች፤</u>**

1) ከሎኔል ደመቀ ዘዉዱ፤ አቶ አታላይ ዛፌ ፤ አቶ መብራቱ ታከለ፤ አቶ ጌታቸዉ አደመ፤ አቶ አለነ ሻማ በአስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ

2) በጎንደርና በኦሮሚያ ወያኔ በፈጠረዉ ህዉከት የታሰሩ ኢትዮጵያዉያን በአስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁነታ ይፈቱ።

3) ጋዜጠኞችና የፖለቲካ መሪወች የሃይማኖት አባቶች ያለምን ቅድመ ሁኔታ ሁሉ በአሸባሪነት ስም ግፍ የተፈጸመባቸዉ ሁሉ በአስቸኳ ይፍቱ

4) በየ አካባቢያችሁ የሚያስተባብሩ የህዝብ አደራ የሚሸከሙ መሪወችን ሕዝቡ ይምረጥ

5) ኢትዮጵያዊያን በአራት ማዕዘን ከወያኔ ሰላዮችና ካድሬወች በቀር ዘርና ሃይማኖት ሳትለያዩ በአንድ ድምጽ ቁሙ

6) ጭቁኑ ሰራዊት ከህዝብ ጎን መቆሙን ማወቅና በሙስና የተዘፈቁ ጀኔራሎችን ለይቶ ማባረር

7) በትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር ድርጅት ያቋቋማቸዉ በሃብት የካበቱ የንግድ ተቋማት የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት መሆናቸዉን አዉቆ በህዝብ ቁጥጥር ስር ማዋል

8) የዘረኛ መሪወች ባንኮችን፤ አንጡራ ሃብቶችን ዘርፈዉ እንዳይጠፉ በያላችሁበት ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ

9) የወልቃይት ጠገዴ/ጠለምት ህዝብን ከቦታዉ ለማስለቀቅ ሰሞኑን ወያኔ የሚያካሂደዉን ዘመቻ ማክሸፍና በአስቸኳይ ቃብቲያን፤ ዳንሻን፤ አዲረመጽን በህዝባዊ ሃይል መቆጣጠር

10) በወያኔ የሙስና ካህናት በኩል የሚያመጣዉን የማዘናጊያ እርቅ አለመቀበል

11) ወያኔ ከስልጣን ካልወረደ ሕዝብን እንደሚጨርስ ማመን

12) የኢትዮጵያ የህዝብ መንግስት ስለሌለ ክፍለ ሃገሩ ህዝቡ መሪዉን መምረጥ

13 የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት መሆኑን አምኖ መደገፍ

14 ለነጻነት የተሰለፈዉ የጎንደር ጀግና ሕዝብ በአጎበር ላይ ብዙ ጥይት ከማባከን እንዲቆጠብ፤ ግን ሽለላ ጀግኖችን ማወደስ ተገቢ መሆኑን ማስገንዘብ

15 የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር አባል የሆነ የታጠቀ ሃይል፤ ካድሬ ወይም ሰላይ ተከዜን ተሻግሮ መግባት በአሁኑ ሰዓት የተከለከለ መሆኑን ለመላዉ ጎንድር/ አማራ ህዝብ ማሳወቅ

ለሟች ቤተሰቦች መጽናናትን እንመኛለን!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!!!!

የጎንደር ህብረት፤